# የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተጠሪ ለሆኑ የሆስፒታሎች አመራር አሰያየምን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 64/2013

**መግቢያ፡-**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ስር የሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋና ወጤታማ አገልግሎት በማቅረብ ህብረተሰቡን ማርካት እንዲችሉ ለማድረግ የሥራ አመራር ተግባራት ብቃት ባለው አመራር እንዲመሩ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የሆስፒታሎችን የህክምና እና የበሽታ መከላከል ተግባራት በጥራትና ተገቢነት ላይ እንዲወል ፣እንዲሻሻሉና እንዲጎለብቱ ለማድረግ በሞያቸው የሰለጡ ብቃት ችሎታና ዕምነት የሚጣልባቸውን ግለሰቦች ወደ አመራርነት እና የአስተዳደር የሥራ ኃላፊነት ለማምጣት በማስፈለጉ፤

የሆስፒታሎች ተቋማዊ ብቃትን ለማሳደግ፣ መልካም አስተዳደርን ማስፈን የሚያስችል የአመራርና የአስተዳደር የሹመት ቦታዎች አቅምን ማዕከል ያደረገ ወድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ፣ አሳታፊ እና ግልፅ የሆነ አሰራር በማስፈን በሆስፒታሎች የሚሾሙ አመራሮች ከአድሎአዊነት በጸዳ ሁኔታ የተሸለ ብቃት ያለው ሰው የማለየት ሂደቱ ተአሚኒነት ያለው እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በሆስፒታሎች በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ሹመትና ምደባ ተግባር ሂደት የእጩ መልማዩና ምርጫ ኮሚቴዎች፣ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ተመርጠው የሚሾሙባቸውን ዓላማዎች፣ ሥርዓቶችና መስፈርቶች ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ጤና ቢሮ በአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15(3) (ሠ)፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፤አስተዳደርና አመራር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/2001 አንቀፅ 31(2) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፤አስተዳደርና አመራር ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 4/2001 በአንቀጽ 38(1) መሰረት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ “ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የሆስፒታሎች የአመራርና ምርጫ ሹመት/ምደባ ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 64/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

2. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1/ “አዋጅ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 8/2001 እና የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 31/2004 ነው፤

2/ ”ደንብ”ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 4/2001 ነው፤

3/ “ቦርድ“ ማለት በአዋጅ ቁጥር 8/2001 መሠረት የሚቋቋም ሆስፒታሎችን/ጤና ጣቢያዎችን በበላይነት የሚያስተዳድር ቦርድ ነው፤

4/ “የተቋሙ አመራር “ ማለት የሆስፒታል ስራ አስኪያጅ፣ ሜዲካል ዳይሬክተር፣ ፕሮቮስትና ም/ፕሮቮስት ፣ በእነዚህ ማዕረጎች ደረጃ የሚሾሙ ኃላፊዎችን ያካትታል፤

6/ “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

7/ “የጤና ተቋማት” ማለት በአዲስ አበባ ከተማአስተዳደር ጤና ቢሮ ስር የሚተዳደር ሆስፒታል ነው፤

8/ “ ቢሮ” ወይም“ቢሮ ኃላፊ” ማለት እንደ ቅደምተከተሉ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ወይምየጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፤

9/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀውሁሉ የሴት ፆታንምያካትታል፤

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቢሮውስር በሚተዳደሩ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያ ላይ ተፈፃሚሆናል፤

## ክፍል ሁለት

## ዓላማ፣የጤና ተቋማት ቦርድና አመራር አሿሿም

4. ዓላማ

1. መመሪያው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ስር ሆስፒታሎች ውስጥ የአመራርነት ቦታዎችን ለማያዝ የሚያስፈልግ ብቃት፣ክህሎት፣ልምድና ባህሪያት ያላቸው ተወዳዳሪና ብቁ የሆኑ ግለሰቦችን ለመቅጠር እንዲያስችል፤

2. ዕጩዎችን ለመምልመል እና ለማፃምም የሚከተሉት ሂደት በግልፅ የሚታወቅ፣የታወቁ ደረጃዎች እና መመዘኛዎችን የተከተለ፣ፍትሀዊ ግልፅ፣ዲሞክራሲያዊ እና ተዓሚነት ያለው ሂደት መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻሉ፤

3. የምልመላና የቅጥር ሥርዓቱ የሚያሻሙ ውጥ፣እና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ከሙስናና ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል፤የሹመትና ምደባ ሥርዓቱ ዕኩልነትና እና ህብረብሄራዊነትን ያከበር እንዲሁም የፆታና የሙያ ስብጥር ያለው ሆኖ እንዲሰራ አቅጣጫ ለማስየት የወጣ ነው፡፡

5. የጤና ተቋማት ቦርድ አሰያየም

1/ የጤና ተቋማት የቦርድ አማራረትና አሰራር ስልጣንና ተግባር በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 8/2001፣ በደንብ ቁጥር 4/2001 እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1/2001 እና የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 31/2004 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6. የጤና ተቋማት አመራሮች አሰያየም

1 መርሆ

በጤና ተቋማት የሚሾሙ አመራሮች አመራረጥና አሰያየም ግልፅና አሳታፊ በሆነ የውድድር ሂደት ተመስርቶ ይፈፀማል፤ ምርጫ ምደባውንም ጾታን፣የሙያ ስብጥርንና ህብረብሄራዊነትን በማመጣጠን ይፈፀማል፤

2 የዕጩ መልማዩና ምርጫ ኮሚቴ ማቋቋም

ሀ/ አምስት አባላት ያሉት የዕጩ መልማዩና ምርጫ ኮሚቴ ይዋቀራል፤

ለ/ የኮሚቴ አባላት ፈቃደኛ የሆኑ፤ በስነምግባራቸው አርአያ የሆኑ፤ኃላፊነታቸውን በሙሉ ቁርጠኝነት፤በፍታሃዊነትና ሃቀኛነት የሚወጡ፤ሚስጥር የሚጠብቁ፤ዕጩዎችን የመምልመል ብቃት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

ሐ/ የዕጩ ምልመላና ምርጫ ኮሚቴ የሚውከሉ ሰዎች የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፤ስለ ክፍት የስራ መደቡ በባህሪይ እና ጥሩ የሚመዛዘን ችሎታና ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

4/ የዕጩ ምልመላና ምርጫ ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመኑ የኃላፊነት ቦታዎች የማሟላቱ ሥራው እንደተጠናቀቀ የሚያበቃ ይሆናል፤

## 7. <u>የምልመላና ምርጫ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃለፊነት</u>

1/ የምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና ፀሐፊው ስብሰባዎችን የሚያዘጋጁ ሲሆን የምልመላ፣የማጣሪያና የምርጫ ሂደት የጊዜ ሰሌዳን ጨምሮ የኮሚቴውን የአሰራር ዘዴዎች ያዘጋጃሉ፤

2/ የኃላፊነት ቦታዎቹ ሃገራዊ ሽፋን ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን በግልፅ እንዲታወቅ ማድረግ፤

3/ የአመልካቾችን መረጃ መዝግቦ መያዝ፤

4/ማስታወቂያ ለወጣባቸው የስራ መደቦች በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን፣ የትምህርት ማስረጃዎችን፣የስራ ልምዶችንና የምስክር ወረቀቶችን መቀበል፤

5/ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተወዳዳሪዎችን መገምገም፣ማነጋገርና ለይቶ ማውጣት፤

6/ እንደአስፈላጊነቱ የወይይትና የግምገማ መድረኮችን ማዘጋጀትና ማመቻቸት፤

7/ የዕጩ ውጤት መግለጫ ስም ዝርዝራቸውን ባገኘው ውጤት መሰረት ማዘጋጀት፤

8/ ለአመራርነት የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መቀበል፤

9/ የምርጫ ሂደቱን መቆጣጠር፤

10/ምርጫውን የሚመለከቱ አጠቃላይ መግለጫ ማቅረብ፤

## 8. <u>የሆስፒታል ሥራአስኪያጅ ፣ፕሮቮስትና ም/ፕሮቮስት ምርጫ አሰያየም</u>

1/የጤና ተቋማት የአመራር ፍላጎትና የስራ መግለጫ (ፕሮፋይል) አዘጋጅተው ብቃት ያላቸው አመልካቾችን በበቂ ቁጥር በሚጋብዝ ሁኔታ አንደአስፈላጊነቱ በወስጥና በውጪ ግልፅ ማስታወቂያ ያስነግራል፤

2/ የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ የሆስፒታል ዕጩ ሥራ ስኪያጅ ይለያል፤

3/ ሦስት የመጨረሻ ዕጩዎችን በማምረጥ እንዲገመገሙ ከመግለጫ ጋር ባስመዘገቡት ውጤት ቅደም ተከተል ለቦርዶ ኃላፊ ያቀርባል፤

4/ የጤና ተቋሙ ስራ አስኪያጅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(4) መሰረት በቦርዶ ኃላፊው ይሾማል፤

## 9. <u>ዕጩ ተወዳዳሪዎችን የምርጫ መስፈርት</u>

ዕጩ ተወዳዳሪዎችን የመምረጫ መስፈርት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ተግባራዊ በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፤

1/ የትምህርት ደረጃ 30 ከመቶ ሆኖ ነጥብ አሰጣጡም ከዚህ በታች በተዘረዘረው ማስረት ይሆናል ህጋዊ ዕውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም፦ –

ሀ/ የህክምና ዶክትሬት ያለው (20ነጥብ)

ለ/ የህክምና ስፔሻሊስት ሀኪም የሆነ (25ነጥብ)

ሐ/የህክምና ዶክትሬት እና በህብረተሰብ ጤና ማስተርስ ዲግሪ ያለው (28ነጥብ)

መ/የህክምና ስፔሻሊስት ሀኪም እና በህብረተሰብ ጤና ማስተርስ ወይም በሆስፒታል አስተዳደር ሁለተኛ ዲግሪ ያለው (30 ነጥብ)

2/ የስራ ልምድ 25 ከመቶ ሲሆን ፤ለስራ መደቡ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ወጤት/ክብደት የሚሰጠው ለእያንዳንዱ አገልግሎት ዘመን ሆኖ ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ ማስርት ይሆናል፡ –

| | | በተለያየ የጤና ተቋማት ላይ በአመራርነት የሰሩበት ጊዜ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በጤና ተቋማት በህክምና አገልግሎት የሰሩበት ጊዜ በዓመት | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6-10 | >11 |
| | 1 | 2.75 | 4.25 | 5.75 | 7.25 | 8.75 | 10.25 | 11.75 |
| | 2 | 4 | 5.5 | 7 | 8.5 | 10 | 11.5 | 13 |
| | 3 | 5.25 | 6.75 | 8.25 | 9.75 | 11.25 | 12.75 | 14.25 |
| | 4 | 6.5 | 8 | 9.25 | 11 | 12.5 | 14 | 15.5 |
| | 5 | 7.75 | 9.25 | 10.75 | 12.25 | 13.75 | 15.25 | 16.75 |
| | 6-10 | 9.25 | 10.75 | 12.25 | 13.75 | 15.25 | 16.75 | 18.25 |
| | >11 | 10.50 | 12 | 13.50 | 13 | 16.50 | 18 | 25 |

3/ የዝግጅት ገለፃ አቀራረብ 25ከመቶ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚማከታቸው አካላት በሚገኙበት /በሚታደሙበት ግልፅ መድረክ ላይ ስለ ፤ርዕያቸውና ስለሚከተሉት አቅጣጫ ገለፃ እያደረጉ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተገምግሞ ወጤት የሚሰጣቸው ይሆናል፤

ሀ/ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ተቋሙን በብቃት ለማሯሯት ያላቸው አቅም፣አዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅ እና ለተገልጋዩ ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለማድረስ፣ ያላቸው ትጋት፣የትንተና እና ስትራቴጂካዊ ክህሎቶች፣ስለ ጤና ተቋሙ ያላቸው ግንዛቤ(5ነጥብ)፤
ለ/ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ገቢ ሊያስገኙ የሚቻሉበትን ችሎታ ክህሎትና ልምድ፤የህዝብ ከበሬታ ፤በቀጣዩ ሊሰሯቸው ያቀዱት (10ነጥብ)
ሐ/ ለጤና ተቋማት ልህቀትና ጥራት መሻሻል ያላቸው ቁርጠኝነት(5ነጥብ)
መ/ በዝግጅት አቀራረብ ያላቸው ጥሩ ተነጋጋሪነት መሳነት እና ግልጽነት (5ነጥብ)
ሠ/ በአመራር ክህሎት እና ብቃት ላይ በፓናል የሚደረግ ቃለ መጠይቅ (20ከመቶ)፡ –

ሀ/ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ የማዘጋጀት የማስፈፀም ችሎታ(5ነጥብ)

ለ/የአገር አቀፍ ፖሊሲዎች ዕውቀትና የአመራርነት ልምድ(5ነጥብ)

ሐ/መልካም ስምና ሀቀኝነት እንዲሁም የግል ተነሳሽነት(5ነጥብ)

መ/የህዝብ ግንኙነት ክህሎት እና የባለድርሻ አካላትን የማስተፍ ክህሎት(5ነጥብ)

4/በዕጩ መልማዩና ምርጫ ኮሚቴ አማካይነት ተሰልቶ የቀረበለትን የተወዳዳሪዎች ወጤት 80 በመቶ እና የራሱን ግምገማ ከ20 በመቶ ጨምሮ በማስላት ከ1ኛ እስከ 3ኛ የሚወጡትን ዕጩዎች ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል፤

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. <u>ቅሬታና አቤቱታ ስለመቀበል</u>

1/ ከስራ አስኪያጁ ምልመላና ምደባ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በቢሮ ኃላፊው የሚስተናገድ ይሆናል፤

2/ በአመራር ምርጫ ምደባ ሂደት ላይ አቤቱታ ያለው ማንኛውም አካል ይግባኝ ማቅረብ የሚችለው ምደባው በተገለፀ በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው፤

3/ ቢሮ ኃላፊው ቅሬታው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው የሚያሳውቅ ይሆናል

11. <u>ከኃላፊነት ስለማሰናበት</u>

ወቅቱን በጠበቀ በስራ አፈፃፀም ግምገማ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ እንዲሁም ህገወጥ ድርጊቶችን ፈፅሞ ሲገኝ ስራአስኪያጁ በቢሮው ኃላፊ አማካኝነት ከኃላፊነቱ ያነሳል፤

12. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ በየደረጃው ያሉ አመራሮች፤ ሠራተኞች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችን የመፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፤

13. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት መመሪያ እና አሰራር በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

14. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ለማሻሻል ይችላል፤

15. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት</u>

ይህ መመሪያ ከ…………../2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዮሐንስ ጫላ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ

አዲስ አበባ